# የመኪና ማቆሚያ፣ የመንገድ ህጎች እና እርስዎ

**የመኪና ማቆሚያ እና የትራፊክ ህጎች ቪክቶሪያ ውስጥ ያሉ መንገዶች ደህንነታቸው የተጠበቀ እና ፍትሃዊ በሆነ መንገድ የሁሉንም ሰው ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የተዘጋጁ ናቸው።**

## የእርስዎ ኃላፊነት

የመንጃ ፈቃድ ያለው አሽከርካሪ እንደመሆንዎ መጠን የመንገድ ደንቦችን ማወቅ እና በማንኛውም ጊዜ እነሱን ማክበር ይጠበቅብዎታል። የመንገድ ደንቦችን አለማክበር የመኪና ማቆሚያ ቅጣት ሊያስጥልብዎ ይችላል። ይህ ቅጣት በጊዜው ካልተከፈለ በሕግ የተደነገጉ ወጪዎች እና በፍርድ ቤት የሚወሰኑ ተጨማሪ ቅጣቶችን ሊያመጣ ይችላሉ።

## የአካባቢ ምክር ቤት ኃላፊነት

የሚከተሉትን ጉዳዮች ማረጋገጥ አለብን

- የመኪና ማቆሚያ ቦታዎች ለሕብረተሰቡ እኩል መጠቀሚያ መሆናቸውን
- የሞተር እና የእግረኞች ትራፊክ አለመስተጓጎሉን ወይም ሳንካ አልባ መሆኑን
- ደህንነቱ ባልተጠበቀ የመኪና አቋቋም ምክንያት ሊከሰት የሚችለውን ማንኛውም አደጋ መቀነስ

## በጣም ለረጅም ጊዜ መኪና ማቆም




በተቻለ መጠን ብዙ ሰዎች ወደ አንድ አካባቢ እንዲደርሱ ለማድረግ በመኪና ማቆሚያ ቦታዎች ላይ የጊዜ ገደቦች ተጥሏል።

የመኪና ማቆሚያ መቆጣጠሪያ ምልክት በመንገዱን ርዝመት ልክ ወይም በተወሰነ አካባቢ ላይ ከተሰቀለ፣ ከተፈቀደው ጊዜ በላይ በአንድ ጊዜ (ያለማቋረጥ) እዚያ ቦታ ወይንም አካባቢ ላይ መኪናዎን ማቆም የለብዎትም።

ይህ ምልክት በትምህርት ቀናት ከጠዋቱ 8 ኤም እስከ ከሰአት በኋላ 5 ፒኤም ድረስ ለ15 ደቂቃዎች ብቻ መኪና ማቆም ይፈቀዳል ማለት ነው።

## መኪናዎን  በትክክል ማቆም

በመኪና ማቆሚያ ቦታ ላይ በተሰመሩት መስመሮች መካከል የግድ መኪናዎን ማቆም አለብዎት። የሚፈቅድ ምልክት ከሌለ በስተቀር አንድ አሽከርካሪ መኪናውን ለብስክሌት በተዘጋጀው መንገድ፣ በእግረኛ መንገድ፣ በተሽከረካሪና እግረኛ የጋራ መንገድ፣ በመንገድ ማከፋፈያ መስመር ወይም በመኖሪያ ስፍራ  አካባቢ ባለ መንገድ አጠገብ በበቀለ ሳር ላይ ማቆም አይቻልም።



**ማቆም ክልክል ነው (No Stopping)** ማለት **በማንኛውም ጊዜ መኪና ማቆም አይቻልም ማለት ነው።** ይህም ማለት  ምንም እንኳን ሰው ከመኪናዎ እያወረዱ ቢሆንም፣ ሞተሩ ባይጠፋም እንዲሁም ከመኪናዎ ባይወርዱም መኪና ማቆም አይቻልም ማለት ነው።

ማቆም ክልክል የሆነበትን አካባቢ የመንገዱን ጠርዝ ቢጫ በመቀባት ሊገለጽ ይችላል



**መኪናን ደርቦ ማቆም ወንጀል ነው።**

ሁለት መኪናዎችን በሚያሳል መንገድ ላይ መኪናዎን በሚያቆሙበት ጊዜ በመንገዱ በግራ በኩል ብቻ ነው ማቆም ያለብዎ። መንገዱ ባለ አንድ አቅጣጫ ካልሆነ በስተቀር መኪናዎን ወደሚሄዱበት አቅጣጫን ፊቱን አዙረው ማቆም አለብዎ፣ ይህም ማለትም የመኪናው መሪ ሳይሆን የተሳፋሪ ወገን በመንገዱ ጠርዝ በኩል መሆን አለበት።

**ወደ ቤት የሚያስገባ የመኪና መንገዶች**





አሽከርካሪዎች ወደ ቤት የሚያስገቡ የመኪና መንገዶችን ዘግተው መኪና ማቆም የለባቸውም እንዲሁም ለእግረኞች መውጫ እና መግቢያ ግልፅ መተላለፊያን መፍቀድ አለባቸው።

አሽከርካሪዎች ተማሪዎችን ለመውሰድ ወይም ለማውረድ ወደ ቤት የሚያስገባ የመኪና መንገዶች ላይ መኪና ማቆም የለባቸውም።

**ተደራሽ (የአካል ጉዳት ላለባቸው ሰዎች የተዘጋጀ) የመኪና ማቆሚያ**




ተደራሽ (የአካል ጉዳት ላለባቸው ሰዎች የተዘጋጀ) የመኪና ማቆሚያ ቦታ መጠቀም የሚችሉት ሰማያዊ በነጭ መደብ በሆነ የአካል ጉዳተኛ የማቆሚያ ፈቃድ ባላቸው ሰዎች ወይም የአካል ጉዳተኛ የመኪና ማቆሚያ ፈቃድ ያለውን ሰው ወደ መኪናው እንዲገባ ወይም እንዲወጣ ለማድረግ መኪናውን በሚያቆም አሽከርካሪ ብቻ ነው። ፈቃዶች የሚሰሩት የአካል ጉዳተኛው ሰው በተሽከርካሪው ውስጥ ሲጓዝ ብቻ ነው።

አሽከርካሪዎች በፖሊስ ወይም በመኪና ማቆሚያ ተቆጣጣሪ ከተጠየቁ ስማቸውን እና አድራሻውን፣ የመንጃ ፈቃዳቸውን እና የማቆሚያ ፈቃዱን ማሳየት አለባቸው።

## የመኪና ማቆሚያ ደህንነት ምክሮች

በልጆችዎ ትምህርት ቤት አካባቢ ባሉ በመንገዶች ወይም በጎዳናዎች ላይ መኪናዎን ካቆሙ፡

1. ልጅዎን በደህና ሁኔታ ወደ ትምህርት ቤት ለመውሰድ በቂ ጊዜ ይመድቡ። ከትምህርት ቤቱ ትንሽ ራቅ ብለው መኪናዎን በማቆም ወደ ትምህርት ቤት በእግርዎ አጭር ርቀት መጓዝን ያስቡበት።
2. ሁሉንም የትራፊክ መቆጣጠሪያ ምልክቶችን እና የትምህርት ቤቱን ማቋረጫ ተቆጣጣሪ የሚሰጡትን መመሪያዎች ይተግብሩ።
3. መቼ እና የት በደህና ሁኔታ ልጅዎትን ከትምህርት ቤት ሊወሰዱ እንደሚችሉ ከልጅዎ ጋር በጋራ ይወያዩ። ከመኪናዎ በደህና ሁኔታ ወጥተው መንገዱን ሊያቋርጡ የሚችሉበትን ቦታ ይምረጡ።
4. ከመንገድ ማዶ ያለውን ልጅዎን መንገዱን እንዲያቋርጥ በጭራሽ አያድርጉ። ለልጅዎ በመንገድ ላይ መሮጥ አደገኛ ነው

- ✓ በመንገድ ላይ እና በትምህርት ቤቱ ዙሪያ የልጆቻችንን፣ የሌሎች እግረኞችን እና የሞተር አሽከርካሪዎችን ደህንነት ማረጋገጥ እንፈልጋለን።
- ✓ ልጆች ለጉዳት ተጋላጭ እና ብዙውን ጊዜ በስሜት የሚነዱ ናቸው። አዋቂዎች ለልጆች ምሳሌ የሚሆን ባህሪ ማሳየት በጣም አስፈላጊ ሲሆን መንገድ በሚሻገሩበት ጊዜ ጥሩ የመንገድ ደህንነት ልምዶችን ማዘጋጀት አስፈላጊ ነው።
- ✓ እባክዎን ለልጆችዎ ደህንነት እና እንዲሁም ለልጆችዎ የክፍል ጓደኞች እና ጓደኞቻቸው ደህንነት እነዚህን ህጎች ይከተሉ
- ✓ እያንዳንዱ ወላጅ እነዚህን ደንቦች ከተከተለ የሁሉም የትምህርት ቤት ልጆች ደህንነቱ የተጠበቀ ይሆናል